# ጤናማ የግብረ ሥጋ ግንኙነት

እርስዎም ሆኑ የወሲብ ጓደኛዎ ስለእርስ በርሳችሁም ሆነ ስለየራሳችሁ ጥሩ የሆነ ስሜት ሲሰማችሁ ጤናማ ግንኙነት ተብሎ ይጠራል። ግንኙነቱ በመከባበር ላይ የተመሰረተ ነው። በ ካናዳ የፍቅር ጓደኛሞች ሁለቱም እኩል ናቸው። ሁለቱም ወሲብን አስመልክቶ ውሳኔ አብረው ይወስናሉ፣ የግብረሥጋ ግንኙነት ለማድረግ ሁለቱም መስማማት አለባቸው፤ የተጋቡም ቢሆን እንኳ አንደኛው ሌላው ወገን ሳይፈልግ ለወሲብ ማስገደድ ከህግ ውጭ ነው፡ ጥሩ ግንኙነት ለጥሩ ጤናማና አስደሳች ህይወት ቁልፍ ነው።

## እራስዎንም ሆነ ጓደኛዎን ከአባለዘር በሽታ ይጠብቁ

ያገቡም ሆኑ ያላገቡ እራስዎንና የወሲብ ጓደኛዎን (ጓደኞችዎን) ከማንኛውም ያባለዘር በሽታ መጠበቅ በጣም አስፈላጊ ነው ይህን ለማድረግ አማራጩ የሚከተሉትን ህጎች ማክበር ነው፡-

- ከግዜያዊ ወሲብ መቆጠብ የትዳር ጓደኛ ወይንም ቋሚ ጓደኛ እስክይዙ ድረስ ከወሲብ ይቆጠቡ። የወሲብ ጓደኛ ሲበዛ በአባለዘር በሽታ መያዝም ሆነ የማስተላለፍ እድሉ በጣም ከፍ ያለ ይሆናል።
- ለጓደኛዎ ፣ ለባለቤትዎ ታማኝ ይሁኑ። ከሌሎች ጋር ወሲብ ከፈጸሙ እራስዎንም ሆነ ጓደኛዎን ለበሽታ ያጋልጣሉ፤ በሽታው ለትዳር ጓደኛዎ ብቻ ሳይሆን ለልጆችዎም ይተርፋል።
- ማንኛውንም አይነት የግብረ ስጋ ግንኙነት ሲያደርጉ ኮንዶም ይጠቀሙ።
- ለአባለዘር በሽታ መድሃኒት እየወሰዱ ከሆነ ወሲብ ከማድረግዎ በፊት ቀድመው መድሁኒትዎን ይጨርሱ።

## ያባለዘር በሽታ እንዴት ይይዛል?

ያባለዘር በሽታ ማንኛውንም ሰው ሊይዘው ይችላል። ወሲባዊ ባልሆነ ግንኙነት በደም ወይንም ከሰውነት በሚወጣ ፈሳሽ በመሳሰሉት ያባለዘር በሽታ ሊተላለፍ ይችላል። አብዛኛውን ግዜ ግን ያባለዘር በሽታ የሚተላለፈው በግብረ ሥጋ ግንኙነት ነው። በካናዳ የወሲብ ጓደኛዎ ኮንዶም እንዲጠቀም መጠየቅ ምንም ነውር የለበትም።

## ያባለዘር በሽታ በካናዳ

ያባለዘር በሽታ በካናዳ የተለመደ ሲሆን ኤች.አይ.ቪ. የተባለው ያባላዘር ቫይረስ ደግሞ ከባድና እስካሁን ፈውስ ላልተገኘለት ኤድስ ለተባለው በሽታ የሚያጋልጥ ነው። የጥናት ተመራማሪዎች እንደሚነግሩን ባሁኑ ግዜ በካናዳ ውስጥ 58 ሺህ ሰዎች ኤች አይ ቪ ያለባቸው ሲሆን አብዛኞቹ ቫይረሱ እንዳለባቸው እንኳ አያውቁም። ማንም ሰው የበሽታው ስሜት ከሌለበት በሽታው እንዳለበት ላያውቅ ይችላል። ስለዚህ አንድ ሰው ኤች አይ ቪ እንዳለበትና እንደሌለበት ስለማይታወቅ እራስን መጠበቅ በጣም አስፈላጊ ነው።

## ለወሲብ ጓደኛ ስለ ኤች አይ ቪ የማሳወቅ ሃላፊነት

በካናዳ ህግ መሰረት ኤችአይቪ እንዳለብዎ ካወቁ በሽታውን ሊያስተላልፍ የሚችል ግንኙነት ከወሲብ ጓደኛዎ ጋር ከማድረግዎ በፊት ስለሁኔታዎ የማሳወቅ ሃላፊነት አለብዎ። በግብረ ሥጋ ግንኙነት ወቅት ኮንዶም የሚጠቀሙ ከሆነ አለመናገር ይችላሉ ሆኖም ግን መናገሩ ጥሩ አማራጭ ነው።

## ስለሁኔታዎ አለማሳወቅ የሚያስከትለው ጠንቅ

ስለሁኔታዎ እያወቁ ሌላን ሰው ለ ኤች አይ ቪ በሽታ አጋልጦ መስጠት በህግ የሚያስቀጣ ወንጀል ነው። ኤች አይቪ እንዳለብዎ እያወቁ ለወሲብ ጓደኛዎ ስለሁኔታዎ ሳያሳውቁ ካለኮንዶም ግብረ ሥጋ ግንኙነት አድርገው ጓደኛዎን ለበሽታው ካጋለጡ በወንጀለኛ መቅጫ ህግ መሰረት ለብዙ አመታት እስር ሊፈረድብዎ ይችላል።

## ለአባለዘር በሽታ መመርመር

ምርመራው በነጻ ሲሆን ለመመርመር ክሊኒክም ሆነ ሆስፒታል መሄድ ይቻላል። ምርመራውም ሆነ ውጤቱ በሚስጥር የሚጠበቅ ነው ። ካስፈለገም በማኒቶባ ውስጥ ስምን ሳይጠቅሱ መመርመር የሚችሉባቸው ሁለት ቦታዎች አሉ፡-

- ናይን ሰርክልስ ኮሚዩኒቲ ሄልዝ ሴንተር(Nine Circles Community Health Center) 705 ብሮድ ዌይ ዊነፔግ የስልክ ቁጥር ( 204) 940- 6000
- ፐብሊክ ሄልዝ ሰርቪስ ዩኒት ኤ (Public Health Services Unit A) 800 ሮሰር አቨኒው ብራንደን የስልክ ቁጥር (204) 571-8483

ከሚከተሉት አሳሳቢ ጉዳዮች አንዱ ከገጠመዎት ለ ኤች አይቪ ና ለአባላዘር በሽታ መመርመር አለብዎ

- የራስዎ ወይም የወሲብ ወዳጅዎ ጤንነት ካሳሰብዎት
- እርስዎ ወይ የወሲብ ወዳጅዎ ከሌላ ሰው ጋር ግብረ ሥጋ ግንኙነት ካደረጋችሁ
- በግንኙነት ወቅት ትጠቀሙበት የነበረው ኮንዶም ከተቀደደ
- ተገደው ከተደፈሩ
- የሌላ ሰው ደም ወይንም የሰውነት ፈሳሽ በድንገት ከነካዎ፤ ለምሳሌ ሌላ ሰው የተጠቀመበትን መርፌ ከነኩ

ተመርምረው ኤች አይ ቪ ቫይረስ እንዳለበዎት ከተረጋገጠ ከዚህ በፊት ከርስዎ ጋር የወሲብ ወዳጅ ለነበሩት በሙሉ የመንገር ሃላፊነት አለብዎ። ውጤትዎ እንኳ በመጀመሪያ ምርመራ ኔጌቲቭ ቢሆን ኤች አይ ቪ መጀመሪያ ደረጃው ላይ ከሆነ ቫይረሱ ስለማይታይ ከጥቂት ወራት በኋላ ደግመው መመርመር ይኖርቦታል።